# <u>ስምንና ታሪክን የለወጠ ጸሎት</u>

**1 ዜና መዋዕል ካልዕ 4፡9-10**

***ያቤጽም ከወንድሞቹ ይልቅ የተከበረ ነበረ እናቱም፡- በጣር ወልጀዋለሁና ብላ ስሙን፦ ያቤጽ ብላ ጠራችው። ያቤጽም፡- እባክህ፥ መባረክን ባርከኝ፥ አገሬንም አስፋው እጅህም ከእኔ ጋር ትሁን እንዳያሳዝነኝም ከክፋት ጠብቀኝ ብሎ የእስራኤልን አምላክ ጠራ እግዚአብሔርም የለመነውን ሰጠው። (1 ዜና መዋዕል 4፡9-10)***

በዚህ ስብከት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙም እውቅና ስለሌለውና ታሪኩ በዝርዝር ስለማይታወቅ ስለ አንድ ሰው እንነጋገራለን። ይህም ሰው ያቤጽ የሚባል ነው። ያቤጽ የሚለው ቃል በሦስት ቦታዎች ማለትም በ 1 ዜና 2፡55፤ 4፡9 እና 4፡10 ላይ ይገኛል። በ 1 ዜና 2፡55 ላይ የምናገኘው ቃል በደቡባዊ ይሁዳ ከቤተልሔም አጠገብ የምትገኝ ከተማ መጠሪያ ነው።

*በያቤጽም የተቀመጡ የጸሐፊዎች ወገኖች ቲርዓውያን፥ ሺምዓታውያን፥ ሡካታውያን ነበሩ እነዚህ ከሬካብ ቤት አባት ከሐማት የወጡ ቄናውያን ናቸው። (1 ዜና 2፡55)*

ይህች ያቤጽ የምትባለው ከተማ ከይሁዳ ወገን የሆኑት ጸሐፍት (የሕጉ አጥኝዎች፣ ጸሐፊዎችና አስተማሪዎች) የሚኖሩባት ከተማ ናት።

በ 1 ዜና 4፡9 እና 10 ላይ የሚገኘው ያቤጽ የሚለው ቃል ደግሞ የሰው መጠሪያ ነው። ምንም እንኳ ያቤጽ ዝርዝር ታሪኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይነገርም በይሁዳ ቤተሰብ ወይም ነገድ ውስጥ የመሪነት ሃላፊነት የነበረው ሰው ነበር።

## I. <u>የያቤጽ ልደት</u>

ከምንባቡ እንደምንመለከተው የያቤጽ እናት ያቤጽን በጣርና በመከራ ስለ ወለደችው ስሙን **<u>"ያቤጽ"</u>** ብላ ጠራችው።

***እናቱም፡- በጣር ወልጀዋለሁና ብላ ስሙን፦ ያቤጽ ብላ ጠራችው። (1 ዜና 4፡9ለ)***

"ያቤጽ" ማለት **<u>"የመከራ ሰው"</u>** ወይም **<u>"የሃዘን ሰው"</u>** ማለት ነው። ያቤጽ የመከራ ወይም የጣር ልጅ ነበር።

- ያቤጽ ገና ከመወለዱ /ከልደቱ/ ጀምሮ የመከራ ገፈት ቀማሽ ነው።

## II. የያቤጽ ስብዕና /ባህርይ/

በክፍሉውስጥ እንደምንመለከተው ያቤጽ ከወንድሞቹና በጊዜው ከነበሩ ከሌሎች ሰዎች ይልቅ የተከበረ ማንነትና ባህርይ የነበረው ሰው ነው።

***ያቤጽም ከወንድሞቹ ይልቅ የተከበረ ነበረ። (1 ዜና 4፡9ሀ)***

ምንም እንኳ ያቤጽ በሃዘንና በጣር የተገኘ የሃዘን ሰው ወይም የጣር ሰው ቢሆንም በሕብረተሰቡ ዘንድ ማለትም በወቅቱ ከነበሩት የይሁዳ ማህበረሰብና ከወንድሞቹ ይልቅ በነበረው መልካም ባህርዩ እጅግ የታወቀ ነበር።

## III. የያቤጽ ስምንና ታሪክን የለወጠ ጸሎት

ከላይ እንደተመለከትነው "ያቤጽ" ማለት **"የመከራ ሰው"** ወይም **"የሃዘን ሰው"** ማለት ነው። ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጊዜ ማንነትን ያመለክታል። ያቤጽ ሃዘንን የሚያስከትል የመከራ ወይም የጣር ልጅ ነበር። ይሁን እንጂ በተግባር ግን ያቤጽ መከራን የሚያመጣ ሳይሆን በመልካም ባህርዩ የታወቀ ሆነ። የዚህ ሰው ስም እንደሚያመለክተው የሃዘን ሰው ከመሆኑ የተነሳ ሃዘን የሚያስከትል እንደሆነ ቢታሰብም ታሪኩ ግን በጸሎት አማካይነት ከስሙ በተቃራኒ ፈጽሞ ተለውጦ እንመለከተዋለን።

- በጸሎት ስማችንና ታሪካችን ይለወጣል።

እንግዲያው የያቤጽን ስምና ታሪክ የለወጠውን ጸሎት እንመልከት።

### 1. ያቤጽ የጸለየው ወደ እግዚአብሔር ነበር።

ያቤጽ የጸለየው ጸሎትን ወደሚሰማ ወደ እስራኤል አምላክ ወደ እግዚአብሔር ነው። "የእስራኤልን አምላክ ጠራ" (1 ዜና 4:10)። ያቤጽ እግዚአብሔር የሚፈልገውን አደረገ።

> ***ወደ እኔ ጩኽ፥ እኔም እመልስልሃለሁ አንተም የማታውቀውን ታላቅና ኃይለኛ ነገርን አሳይሃለሁ። (ኤር 33፡3)***
> ***ወደ እግዚአብሔርም በጮኽን ጊዜ ድምፃችንን ሰማ*** *(ዘሁልቁ 20፡16)*
> ***እግዚአብሔርም የእስራኤልን ድምፅ ሰማ*** *(ዘኁልቁ 21፡3)*

እውነተኛ ጸሎት በሰዎች ዘንድ የጸሎት ሰዎች እንደሆንን ለማስመስከር ወይም ለማሳየት የምናደርገው ልፍለፋ ሳይሆን ልብን ወደ እግዚአብሔር በስውር ማፍሰስ ነው። በእግዚአብሔር ተደጋፊዎች እንደሆንን የምናረጋግጥበት ጩኸት ነው። ከእግዚአብሔር እርዳታና ጸጋ ውጭ በራሳችን ምንም ማድረግ እንደማንችል በማወቅና በመቀበል ለራሱ ለእግዚአብሔር ማንነታችንን የምንገልጽበት መንገድ ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ደግሞ እንደ ተስፋ ቃሉ እንዲህ ዓይነቱን ጸሎት የሚሰማና ጸሎትን የሚመልስ አምላክ ነው።

## 2. <u>የያቤጽ የጸሎቱ ባህርይ ምን ይመስል ነበር?</u>

የያቤጽን ጸሎት ስንመለከት ትህትናና እውነተኛነት የተሞላ ጸሎት ነበር። **<u>"እባክህ"</u>** የሚለው ቃል እውነተኛ የሆነ ተማጽኖን ያመለክታል። ይህ ቃል **<u>"ካልባረክኸኝ አልለቅህም"</u>** ያለውን የያዕቆብን (የእስራኤልን) ጸሎት ያስታውሰናል (ዘፍ 32፡26)። እውነተኛና ከልብ የሆነ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር መድረሱ አጠያያቂ አይደለም።

አሁን ባለንበት ጊዜ እኛም ወደ እግዚአብሔር **<u>"እባክህ"</u>** ብለን የምንጮህባቸው ብዙ ጉዳዮች አሉን። ስለ ሀገራችን፣ ቤተ ክርስቲያናችን፣ ወንጌል ስላልሰሙት ሰዎች፣ ስለ ወጣቶችና አረጋውያን፣ ስለ ልጆች፣ ስለ ራሳችን፣ ወዘተ እባክህ እያልን የምንጮህባቸው ጉዳዮች አሉንና ለእኛም እግዚአብሔር የያቤጽን የተማጽኖ መንፈስ ይስጠን።

## 3. <u>የያቤጽ የጸሎቱ ፍሬ ነገር ምን ነበር?</u>

በያቤጽ ጸሎት ውስጥ አራት ዋነኛ ሀሳቦች አሉ፡-

**ሀ) <u>እግዚአብሔር እንዲባርከው ጸለየ።</u>**

ያቤጽ ምናልባትም እግዚአብሔር ለአብርሐም የሰጠውን ቃል ኪዳን በሚገባ ሳይረዳ አይቀርም።

> ***በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ፥ ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብትና በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ ዘርህም የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል። (ዘፍ 22፡17)***

ስለዚህ ይህን ስንመለከት ያቤጽ እንዲህ ማለቱ ነው፡- የአብርሃም በረከት በእኔ ላይ ይውረድ። ይህ በረከት ደግሞ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ የሚመጣ መንፈሳዊ በረከት ነው።

> ***በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፥ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ። (ያዕ 1፡17)***

ይህ በረከት ስጋን፣ መንፈስንና ነፍስን የሚያረካ መለኮታዊ በረከት ነው። ለእኛም ይህ የአብርሃም በረከት ያስፈልገናል። ይህ የማያቋርጥ የበረከት ምንጭ የሚገኘው በክርስቶስ በኩል ነው።

> ***የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል፥ የአብርሃም በረከት ወደ አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ። (ገላ 3፡14)***
> ***በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ። (ኤፌ 1፡3)***

*ወደ እናንተም ስመጣ በክርስቶስ በረከት ሙላት እንድመጣ አውቃለሁ። (ሮሜ 15፡29)*

እግዚአብሔር የባረካቸው ይባረካሉ! የእግዚአብሔር በረከት ተጨባጭ ስለሆነ ተጨባጭ ውጤት ያስከትላል።

*ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ ለበረከትም ሁን። (ዘፍ 12፡2)*

ለ) **እግዚአብሔር አገሩን (ግዛቱን/ዳርቻውን) እንዲያሰፋለት ጸለየ።**

ይህ ጥቅስ የግድ ግዑዙን መሬት (ምድር) ብቻ የሚያመለክት አይደለም። የያቤጽ ፍላጎት እግዚአብሔር የይሁዳን መልክዓ ምድር በመለጠጥ እንዲያሰፋለት አይደለም። ይህ ክፍል ከመጀመርያው ጸሎት ማለትም ከበረከት ጋር የተያያዘ ነው። ያቤጽ እግዚአብሔር በየትኛውም አቅጣጫ ነገሮችን ሁሉ እንዲያሰፋለትና እንዲያበዛለት፤የበረከቱም ዳርቻ ሁሉን የሚያካትት እንዲሆንለት ያደረገው ጸሎት ነው።

- ልቡ እንዲሰፋለት፣ አስተሳሰቡ፣ አመለካከቱ፣ እይታው፣ ራዕዩ፣ ወዘተ እንዲሰፋለት
- የሚሰራው ስራ እንዲሰፋለት
- አገልግሎቱ እንዲሰፋለት፣ በአገልግሎቱም የእግዚአብሔር መንግስት ዳርቻ እንዲሰፋለት
- ያ በክርስቶስ በኩል የሚመጣው መለኮታዊ በረከት ለሌሎች ባሉበት ስፍራ ሁሉ እንዲደርስ
- እግዚአብሔር በኪዳኑ በኩል በሰማይ ያዘጋጀለት መለኮታዊ ድርሻውን እንዲያበዛለት
- መንፈሳዊ ሕይወቱ የተትረፈረፈ እንዲሆንለት

የይስሐቅም ታሪክ የሚያሳየን ይህንን እውነት ነው። እግዚብሔር በእርሱ ለሚታመኑትና ለሚደገፉበት በእውነትም ሁለንተናዊ ሕይወታቸውን ያሰፋል፣ ያበዛል።

*ይስሐቅም በአባቱ በአብርሃም ዘመን ቈፍረዋቸው የነበሩትን የውኃ ጕድጓዶች ደግሞ አስቈፈረ አብርሃም ከሞተ በኋላ የፍልስጥኤም ሰዎች ደፍነዋቸው ነበሩና አባቱም ይጠራቸው በነበረው ስም ጠራቸው። የይስሐቅ ሎሌዎችም በሸለቆው ውስጥ ቈፈሩ፥ በዚያም የሚመነጭ የውኃ ጕድጓድ አገኙ። የጌራራ አገር እረኞች ከይስሐቅ እረኞች ጋር፦ ውኃው የእኛ ነው ሲሉ ተከራከሩ የዚያችንም ጕድጓድ ስም ኤሴቅ ብሎ ጠራት፥ ለእርስዋ ሲሉ ተጣልተዋልና። ሌላ ጕድጓድም ማሱ፥ ስለ እርስዋም ደግሞ ተጣሉ ስምዋንም ስጥና ብሎ ጠራት። ከዚያም እልፍ ብሎ ሌላ ጕድጓድ አስቈፈረ፥ ስለ እርስዋም*

*አልተጣሉም ስምዋንም __ርኆቦት__ ብሎ ጠራት እንዲህ ሲል፦ __አሁን እግዚአብሔር አሰፋልን፥ በምድርም እንበዛለን።__ (ዘፍጥረት 26፡18-22)*

**ሐ) __የእግዚአብሔር እጅ ከእርሱ ጋር እንድትሆን ጸለየ።__**

ይህ ጸሎት ከላይ ከተመለከትናቸው ከሁለቱ ጸሎቶች ጋር የተያያዘና የተቆራኘ ነው። መለኮታዊ በረከትን ለማግኘትና ድንበራችንና ዳርቻችን በሁሉ አቅጣጫ እንዲሰፋ ካስፈለገ የእግዚአብሔር ብርቱ እጅ ከእኛ ጋር መሆኗ አማራጭ የሌለውና መተኪያ የማይገኝለት ጉዳይ ነው። ያቤጽም የእግዚአብሔር እጅ ከእርሱ ጋር እንድትሆን የጸለየው ለዚህ ነው። እጅ ብርታትን፣ ችሎታን፣ ስልጣንን፣ ሐይልን፣ ወዘተ የሚያመለክት ነው። የእግዚአብሔር እጅ ደግሞ በባህርይዋ ልዩ ናት። ይህንን እውነት ደግሞ የእስራኤል መሪዎችና የእስራኤል ሕዝብ በተለያዩ ጊዜያቶች በአንደበታቸው በግልጽ መስክረዋል።

**__የእግዚአብሔር እጅ፡-__**

- ብርቱ ናት!

እግዚአብሔር በብርቱ **እጅ** ከግብፅ አውጥቶሃልና (ዘጸ 13፡9 - ሙሴ)
እግዚአብሔር በብርቱ **እጅ** ከባርነት ቤት ከግብፅ ምድር አወጣን (ዘጸ 13፡14)።

- ከፍ ያለች ናት!

የእስራኤልም ልጆች ከፍ ባለች **እጅ** ወጡ። (ዘጸ 14፡8)

- ታላቅ ናት!

እስራኤልም እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ ያደረጋትን ታላቂቱን **እጅ** አዩ፥ ሕዝቡም እግዚአብሔርን ፈሩ፥ በእግዚአብሔርም በባሪያውም በሙሴ አመኑ። (ዘጸ 14፡31)

- የሚያስፈልገንን የምታዘጋጅና ምትባርክ ናት!

የአምላኩም የእግዚአብሔር እጅ በእርሱ ላይ ነበረችና ንጉሡ የሻውን ሁሉ ሰጠው። (ዕዝራ 7፡6)

- መልካም ናት!

መልካሚቱም የአምላኩ እጅ በእርሱ ላይ ነበረችና (ዕዝራ 7፡9)

- የሕዝቡንና የራሱን ጠላቶች የምታደቅቅ ናት!

የአምላካችን **እጅ** በሚሹት ሁሉ ላይ ለመልካም ነው ኃይሉና ቍጣው ግን እርሱን በሚተዉ ሁሉ ላይ ነው (ዕዝራ 8፡22)

- ልዩ መንፈሳዊ ልምምድ ውስጥ እንድንገባ የምታደርግ ናት!

የእግዚአብሔርም **እጅ** በላዬ ነበረ እግዚአብሔርም በመንፈሱ አወጣኝ (ሕዝ 37፡1)

የእግዚአብሔር እጅ ከእኛ ጋር የምትሆነው ለምንድን ነው?

- ለመምራት
- ለመጠበቅ
- ሃይልና ብርታት ለመስጠት
- ስራችንን/አገልግሎታችንን በመስራት ለስኬት
- ወዘተ

የእግዚአብሔር እጅ ብቻ ለእኛ በቂ ናት። ሌላ እጅ አያስፈልገንም። ብቻ የእግዚአብሔር እጅ ከእኛ ጋር ትሁን!

*መ) እግዚአብሔር ከክፉ እንዲጠብቀው ጸለየ።*

*ለመሆኑ ይህ ክፉ የተባለው ምንድን ነው?*

- የኃጢአት ክፋት ነው
- የችግርና የመከራ ክፋት ነው
- የቅዱሳንና የእግዚአብሔር ጠላት የሆነው ዲያብሎስና ሰራዊቱ ክፋት ነው

የመከራ ሰው፣ የሃዘን ሰው፣ የጣር ሰው የተባለው ያቤጽ የጸለየው እግዚአብሔር ከእነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ክፉዎችና ክፋታቸው እንዳይጎዱትና በሕይወቱ ክፋት እንዳያደርጉበት እግዚአብሔር እንዲጠብቀው ነው።

***"እንዳያሳዝነኝም ከክፋት ጠብቀኝ" (ቁ. 10)*** ከሚለው ቃል እንነደምንመለከተው ክፋት ሰውን ሃዘን ውስጥ የሚያስገባ ነው፣ የሃዘን ሰው የሚያደርግ ነው። ይሁን እንጂ ያቤጽ ከስሙ በተቃራኒ እግዚአብሔር ጥበቃውን እንዲያደርግለትና ከሃዘን ሕይወት እንዲጠብቀው ጸለየ። ይህ የእግዚአብሔር ጥበቃ ደግሞ የተስፋ ቃል ያለው እውነት ነው።

> ***ክፉ ነገር ወደ አንተ አይቀርብም፥ መቅሠፍትም ወደ ቤትህ አይገባም። በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና፣ እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል። በተኵላና በእባብ ላይ ትጫማለህ አንበሳውንና ዘንዶውን ትረግጣለህ። በእኔ ተማምኖአልና አስጥለዋለሁ ስሜንም አውቆአልና እጋርደዋለሁ። ይጠራኛል እመልስለትማለሁ፥ በመከራውም ጊዜ ከእርሱ ጋራ እሆናለሁ አድነዋለሁ አከብረውማለሁ። ረጅምን ዕድሜ አጠግበዋለሁ፥ ማዳኔንም አሳየዋለሁ። (መዝ 91፡11-16)***

ስለዚህ እኛም ስለራሳችን፣ ስለቤተ ክርስቲያናችን፣ ስለ ሀገራችን፣ ስለ ቅዱሳን፣ ስለ ሀገር መሪዎችና ባለስልጣናት፣ ወዘተ ልንጸልይ ይገባናል።

### *4. የያቤጽ የጸሎቱ ውጤት ምን ነበር?*

የያቤጽ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ከመድረሱ የተነሳ እግዚአብሔር ልመናውን ሰጠው።

*እግዚአብሔርም የለመነውን ሰጠው። (ቁ. 10)*

እንደ እግዚብሔር ፈቃድ የሆነ ጸሎት ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ መልስ ያገኛል። ያቤጽ እንደ ስሙ የሃዘን ሰው፣ የሰቆቃ ሰው፣ የጉስቁልና ሰውና የእነዚህም ምክንያት አልሆነም። እግዚአብሔር ጸሎቱን በመስማቱ የለመነውን ሁሉ ሰጠው። በአስደናቂ ሁኔታ እግዚአብሔር ስለባረከው እንደ ስሙ ሳይሆን ከስሙ በተጻራሪ መልኩ በበረከት ሞላው፣ ለሌሎችም የበረከት ምክንያት በመሆን ኖረ። በጉዞው፣ በሚይዘውና በሚሰራው ነገር ሁሉ የተባረከ ሆነ።

እኛም እንደ እግዚአብሔር ቃል ለመኖር ራሳችንን በመስጠትና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በመጸለይ የያቤጽን ስምና ታሪክ ወደለወጠው ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ። የተስፋን ቃል የሰጠው እግዚብሔር የታመነ ስለሆነ እርሱ በራሱ መንገድ ይባርከናል። እርሱ ሁለንተናችንን ማትም ሕይወታችንን፣ ትዳራችንን፣ አገልግሎታችንን፣ ቤተሰባችንን፣ ልጆቻችንን፣ ቤተ ክርስቲያናችንን፣ አገራችንን፣ መሪዎቻችንን፣ ሕዝባችንን፣ ወዘተ ይባርካል።

እግዚአብሔር መባረክ ይችላል። ምናልባት የምንጠራበትና የምንታወቅበት የያቤጽ ዓይነት ስም ሰዎች ቢሰጡንም እግዚአብሔር ግን ስማችንና ታሪካችንን መለወጥ ይችላል። አሜን!!